# ኢትዮጵያ ከተጋረጠባት አደጋ ተርፋ ሰላምን ታስቀድም ይሆን?

አህመድ ሶሊማን - ሪሰርች ፌሎው - ሮያል ኢንስቲትዩት ኦፍ ኢንተርናሽናል አፌይርስ (ቻትሃም ሃውስ)



በኢትዮጵያ የተከሰተው አስከፊ የእርስ በእርስ ጦርነት ሁለተኛ አመቱን ይዟል። በፌደራል መንግስቱና በአዲስ መልክ ራሱን የትግራይ መከላከያ ሃይል ብሎ በሰየመው ሃይል መሃከል የቀጠለው ግጭት ትግራይን ተሻግሮ ሌሎች ክልሎችን የገፈቱ ቀማሽ ማድረጉን ተያይዞታል። ግጭቱ በትግራይና በአማራ ልሂቃን መሃከል የነበረውን ቁርሾ እንደ አዲስ ያጋመው ሲሆን በኦሮሚያ፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝና በአፋር ክልሎችም ማንነትን መሰረት ላደረገው ጅምላ ጥቃት ከፍተኛ አበርክቶ ነበረው።

ጦርነቱ ወደ መዲናይቱ አዲስ አበባ በእጅጉ እየተጠጋ ይገኛል። ይሄንንም ተከትሎ ጠ.ሚ አብይ በአካል በጦርነቱ ለመሳተፍ መወሰናቸውን አሳውቀው ስልጣናቸውን በጊዜያዊነት ለምክትል ጠ.ሚ ደመቀ መኮንን አስረክበዋል። ከግጭቱ መናርና ካላባራው ሰብአዊ ቀውስ ጋር ተያይዞ አለም አቀፍ ድርጅቶችና የተለያዩ ዲፕሎማቲክ ሚሲዮኖች ዜጎቻቸው በአስቸኳይ ኢትዮጵያን ለቀው እንዲወጡ መወትወታቸው የየእለት ዜና ወደመሆን አሸጋግሮታል። እ.አ.አ በኖቬምበር 2 ሀገሪቱ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ያወጀች ሲሆን ከአዋጁ ጋር ተያይዞ ማንነትን መሰረት ያደረገ ጥቃትና ወከባ በተለይም በትግራይ ተወላጆች ላይ ቀጥሎ ይገኛል።

በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ ካለፈው ጥቅምት ወዲህ የመጀመሪያው የሰብአዊ ድጋፍ ወደ ትግራይ በቅርቡ ቢደርስም የሰብአዊ ድርጅቶች መረጃ እንደሚያሳየው የእርዳታ ስራውን ለማሳለጥና የተጎዱ ወገኖችን ለመድረስ ቢያንስ 100 ከባድ መኪኖች በየቀኑ የእርዳታ ቁሳቁሶችን ማቅረብ ይገባቸው ነበር።

በተጨማሪም በተባበሩት መንግስታትና በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን ትብብር የተደረገው የሰብአዊ መብት ምርመራ እንደሚያመለክተው በትግራዩ ጦርነት አስከፊ የሰብአዊ መብት ጥሰት፣ ስቅየት እንዲሁም የወሲብ ጥቃት በንጹሃን ላይ በግጭቱ ተዋንያን (በኢፌዴሪ መከላከያ ሰራዊት፣ በትግራይ መከላከያ ሃይል፣ በኤርትራ ሃይሎችና በአማራ የጸጥታ አካላት) የተፈጸመ ሲሆን አንዳንዶቹ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች በሰው ልጆች ላይ የተፈጸሙ ወንጀሎች ዘርፍና በጦርነት ወንጀሎች በአለም አቀፍ ደረጃ የሚያስከስሱ እንደሆኑ ተመልክቷል።

## የትግራይ ሃይሎች ማየልና ግቡ እስካሁን ያልለየለት የመጨረሻ ግባቸው

ባለፉት ጥቂት ወራት የመንግስት ሃይሎች በማፈግፈግ ላይ ተጠምደው ከርመዋል። የትግራይ ሃይሎች ብዙ አካባቢዎችን በአማራና አፋር ክልሎች የተቆጣጠሩ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ ወልድያ፣ ደሴ እንዲሁም ኮምቦልቻ ለአብነት ይጠቀሳሉ። ራሱን የኦሮሞ ነጻነት ግንባር ሰራዊት (ኦነግ) ብሎ ከሚጠራው አማጺ ቡድን ጋር ያሰሩት የአብሮ እንስራ ስምምነት ለዚህ ድል አስተዋጽኦ ያደረገ ሲሆን የኦነግ ሰራዊት በቅርብ ሳምንታት ውስጥ አያሌ ቦታዎችን ሲቆጣጠር በተወሰነ አካባቢም የመንግስት የጸጥታ አካላት ወደዚህ ቡድን የፈለሱበት ሁኔታ ተስተውሏል። መረጃዎች እንደሚያሳዩት የሁለቱ ቡድኖች ጦር በአሁኑ ሰአት ከአዲስ አበባ ከ200 ኪ.ሜ ባነሰ ርቀት ላይ ይገኛሉ። በተለያዩ የአፋር አካባቢዎች ሁለቱ ቡድኖች የኢትዮ ጅቡቲን መስመር ለመቁረጥ ሙከራ እያደረጉ የሚገኙ ሲሆን ይህም በፌደራል መንግስቱ ላይ ጫናቸውን ለማበርታትና በተለይም በትግራይ የሰብአዊ እርዳታ ለማሳለጥ እንደሚጠቅም ያምናሉ። በዚህም ምክንያት ከፌደራል እና ከአፋር ሀይሎች ከባድ ተቃውሞ ገጥሟቸዋል።

ነገር ግን አሁንም የትግራይ ሃይሎች የመጨረሻ ግብ ግልጽ አይደለም። እስካሁን ድረስ የአብይን መንግስት ‹ከመቅጣት› በዘለለ ግልጽ የሆነ የፖለቲካ አላማም ይሁን ሁሉን አሳታፊ የፖለቲካ ጥምረት ለመፍጠር እያደረጉ ያሉት እንቅስቃሴ እምብዛም ነው። በቅርቡ በሃገረ አሜሪካ ህወሃትንና ኦነግን ጨምሮ 9 የሚሆኑ የፖለቲካ ቡድኖች ጥምረታቸውን እወቁልን ያሉ ሲሆን አብዛኞቹ ስብስቦች አነስተኛ ከመሆናቸውም በላይ ብዙ የህብረተሰብ ክፍልን የሚወክሉ ቡድኖች እስካሁን የስብስቡ አካል አልሆኑም። እስካሁንም ድረስ የህወሃት/ትግራይ መከላከያ ሃይል የመጨረሻ ግብ ተመልሶ ስልጣን መቆናጠጥ ይሁን የትግራይን ራስ ገዝ በኮንፌደሬትድ ኢትዮጵያ ማረጋገጥ ይሁን የትግራይ ሙሉ ነጻነት እስካሁን በውል አልለየለትም።

እውነት ለመናገር ጠ.ሚ አብይ አህመድ ገታራ አቋምና ሁሉን ችግር በጦር ሃይል የመፍታት ዝንባሌ የቀጠለ ሲሆን በቅርቡ እንኳን በተደጋጋሚ ጊዜ ህዝባቸውን ወደ ትጥቅ ትግሉ በገፍ እንዲቀላቀል ሲወተውቱ ከርመዋል። ይባስ ብለው ባለፉት ጥቂት ቀናት ራሳቸው ወደ ግምባር እንደሚዘምቱ ያሳወቁ ሲሆን የት ግንባር እንደሚሰለፉ ከመግለጽ ግን ተቆጥበዋል። ምንም እንኳ በመዲናይቱ አዲስ አበባና በተወሰኑ አካባቢዎች ጠ.ሚሩ ያላቸው ድጋፍ የሚናቅ ባይሆኑም የጠ.ሚሩ ተጽእኖ በተለያዩ አካላት እየተሸረሸረ እንደሚገኝ የአደባባይ ሚስጥር ነው። ለዚህም በጦርነቱ ቀጥተኛ ተሳትፎ ያላቸው የክልል መንግስታት የራሳቸውን ሃይል የሚመሩ ሲሆን የሚያስቀድሙትም ክልላዊና ብሄር ተኮር አጀንዳ ሲሆን አላማቸውም የራሳቸውን የወደፊት ሃይል አሰላለፍና ተጽእኖ መጨመር እንጂ የሃገሪቱ የግዛት አንድነት እንዳልሆነ በተደጋጋሚ ተስተውሏል። ይህም ከድህረ ትግራይ ግጭት የሚዘል ቋሚ የግጭት ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ሳይታለም የተፈታ ነው፡ ፡

## አነስተኛ አለም አቀፍ ተጽእኖ/አቅም

ሁሉም የግጭቱ አካላት ለሰላም የሚደረጉ ጥረቶችን ጆሮ ዳባ ልበስ እንዳሉ እየተስተዋለ ይገኛል። ጠ.ሚ አብይ አለም አቀፉ አካላት እርሳቸውን ለማስወገድ የቆረጡ እንደሆነ የሚያምኑ ሲሆን ማሸነፍ የመጨረሻ አማራጫቸው እንደሆነ አጥብቀው ያምናሉ። የህወሃት ሃይሎች ራሳቸው ከቅርብ ጊዜ ድሎቻቸው ወዲህ የሰላም ጥሪዎችን ገሸሽ የማድረግ አዝማሚያ አሳይተዋል። ሁሉም አካላት እርስ በርሳቸው ደመኛ ጠላት እንደሆኑ ማሰብ በስፋት የሚታይ ሃቅ ነው።

አሜሪካና የአውሮፖ ህብረት የተወሰኑ ማእቀቦችን በመጣል የግጭቱ አካላት ወደሰላም ጎዳና እንዲመለሱ ጥረዋል። ከዚህም በስፋት የሚጠቀሰው በመሪዎች ደረጃ የተጣለው የጉዞ እገዳ፣ የእርዳታ ክልከላና የአጎዋ ተጠቃሚነት ላይ የተቀመጡ ማእቀቦች እንደምሳሌ ይጠቀሳሉ። በቅርቡ እንኳን አሜሪካ በኤርትራ ሃይሎች ላይ በትግራዩ ግጭት ጋር በተገናኘ ማእቀብ ያሳለፈች ሲሆን በኢትዮጵያ አካላት ላይም እርምጃ ለመውሰድ ወቅታዊውን የድርድር ጥረት ውጤት እንደምትጠብቅ አስታውቃለች። ችግሩ ተጨማሪ እርምጃዎች በተለይም በመንግስት ላይ የተፈለገውን ውጤት ከማምጣት ይልቅ ብሄርተኝነትን ለማነሳሳት ሲውል በስፋት ይታያል።

ግልጽ በሆነ መልኩ የድርድር አስፈላጊነት ፍንትው ብሎ ወጥቷል ነገር ግን አሁንም ማን በብቃት ይህንን ሚና ይወጣ የሚለው አልተመለሰም። የአፍሪካ ህብረቱ መልእክተኛ የቀድም የናይጀሪያ ፕሬዚደንት ይሄንን ሚና ለመወጣት ተፍ ተፍ እያሉ የሚገኙ ሲሆን ነገር ግን ተጨማሪ የሰውና የገንዘብ ድጋፍ እንደሚያስፈልጋቸው እሙን ነው። የአፍሪካ ህብረት ራሱ አጣብቂኝ ውስጥ ገብቷል። የህበረቱ መቀመጫ አዲስ አበባ እንደመሆኗ መጠን የህብረቱ ተጽእኖ በኢትዮጵያ ላይ አነስተኛ ከመሆኑም በላይ የህብረቱ ውሳኔዎች የህብረት ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው እንደመሆኑ መጠን ህብረቱ ኢትዮጵያን እስከማገድ የሚደርስ እርምጃ የመውሰዱ ሁኔታ በእጅጉ ያነሰ እንደሆነ በስፋት ይታያል። የምስራቅ አፍሪካ በይነ መንግስታት ህብረት የሆነውም ኢጋድ በሱዳን በተፈጠረው ቀውስ ምክንያት እግር ተወርች ታስሮ ይገኛል። ከሱዳኑ ቀውስ ቀደም ብሎም በካርቱምና አዲስ አበባ በድንበር ውዝግብና በአባይ ግድብ ምክንያት የተፈጠረው እሰጥ አገባ የኢጋድን አቅም የቀነሰው ሲሆን በወቅቱ የኢጋድ ጸሃፊና ጠ.ሚ አብይ ዘንድ ያለው ጥብቅ ቁርኝት የኢጋድን ሃላፊነቱን የመወጣት አቅም በእጅጉ ገድቦት ይገኛል።

በዚህ በስፋት በሚታይ ትልቅ ክፍተት መሃል የከባቢው ሃገሮች መሪዎች ሚና በተለይም የኬንያው ኡሁሩ ኬንያታ አስተዋጽኦ በእጅጉ አስፈላጊ ይሆናል። የወቅቱ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የጸጥታ ምክር ቤት ተለዋጭ አባል ኬንያ በተደጋጋሚ ጊዜ ኢትዮጵያ ከአለም አቀፍ ማእቀብ የታደገቻት ሲሆን የኢትዮጵያ ቀውስ በአፍሪካ መር የግጭት አፈታት ዘዴ ሊፈታ እንደሚገባ ስትወተውት ከርማለች። በሌላ መልኩ ግን በሰብአዊ መብቱ ምስቅልቅልና የግጭቱ ተዋንያን የሰላምን መንገድ እንዲመርጡ በማሳሰብ ደረጃ ኬንያ ቀድሞ ተሰላፊነቷን አስመስክራለች። በቅርቡ እንኳን የአሜሪካው ውጪ ጉዳይ ሚኒስትር አንቶኒ ብሊንከን ከኬንያው ኡሁሩ ጋር በኢትዮጵያ ጉዳይ የመከሩ ሲሆን ፕሬዚደንት ኡሁሩ ቀደም ብለው ከጠ.ሚ አብይ ጋር ሰፊ ንግግር ማድረጋቸው የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው። ከዚህ በተጨማሪም የደቡብ አፍሪካው ሲሬል ራማፖዛ የራሳቸውን ጥረት እያደረጉ እንደሚገኙ ምንጮች ይጠቁማሉ።

## እውነተኛ ውይይትና እርቅ በኢትዮጵያ

የተኩስ አቁም ስምምነት የሚኖር ከሆነ እጅግ አስፈላጊ በሆነው የቀጣይ የሀገሪቱ ሁኔታ ላይ የሚወስን ፍኖተ ካርታ ላይ ለመወያየት እድል ይሰጣል። ለዚህም በዋነኛነት የፌደራል መንግስቱም ሆነ ተቃዋሚዎች እርስ በእርስ እውቅና መሰጣጠት ይገባቸዋል። ለዚህም መንግስት በህወሃትና ኦነግ ሸኔ ላይ ያሳለፈውን የሽብርተኝነት ብያኔ ማንሳት የሚገባው ሲሆን በአንጻሩም እንዚህ ቡድኖች ለመንግስቱ እውቅና ሊሰጡት ይገባል። በተመሳሳይ የፌደራሉና የክልል መንግስታት የእርዳታ እንቅስቃሴው እንዳይታጎል ማድረግ የሚገባቸው ሲሆን የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሚያቀናጀው ክትትልና ቁጥጥር ኮሚሽን የተኩስ አቁሙን ለመከታተል ሊቋቋም ይገባል።

በመቀጠልም ተደራዳሪዎቹ በዝርዝር ጉዳዮች ማለትም ለአከራካሪ የታሪክ ትርክቶች፣ የስልጣን ክፍፍል፣ ራስን በራስ የማስተዳደር መብቶች እንዲሁም የውስጣዊ ድንበር ጉዳዮች በስፋት መነጋገር ይገባቸዋል። ይሄም የሀገሪቱን እድሜ ጠገብ ቅራኔዎች ለመፍታት አይነተኛ አማራጭ ከመሆኑም በዘለለ የሃገሪቱን የግዛት አንድነትና ሰላም ለማረጋገጥ የፖለቲካ መሪዎችና ልሂቃን አይነተኛ አስተዋጽኦ ማበርከት የሚገባቸው ታሪካዊ ወቅት ላይ እንደሚገኙ መረዳት ይገባቸዋል። ሰብአዊ እርዳታ በአስቸኳይ ለትግራይ የሚደርስበት ሁኔታም ሊመቻች ይገባል።

የኢትዮጵያ ችግሮች ሊፈቱ የሚችለው በድርድርና ሁሉን አሳታፊ በሆነ የሽግግር ሂደት ብቻ ነው። በሰላም ሚኒስትርና በሌሎች ሃገር በቀል ድርጅቶች የተመሰረተው ማይንድ ኢትዮጵያ ከጥንስሱ ጀምሮ በተዋረዳዊ

ችግሮች የተተበተበ ሲሆን በአባል ድርጅቶቹ መሃከል ያለው ኢ-ጤናማ ግንኙነት በውጤታማነቱ ላይ ጥላ አጥልቶበታል። አዲስ የሚቋቋመው የእርቅ ኮሚሽን ከመንግስት ተጽእኖ ራሱን ነጻ ማውጣትና መስፋት እንዲሁም የመንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሚና የሚዳብርበት መድረክ ሊሆን ግድ ይላል።

የሽግግር ሂደቱ በእስር የሚገኙ የተቃዋሚ መሪዎችን ማለትም ጃዋር መሃመድ፣ በቀለ ገርባንና እስክንድር ነጋን ጨምሮ ሌሎችንም አሳታፊ ማድረግ የሚገባው ሲሆን በተጨማሪም መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የሃይማኖት መሪዎችና ታዋቂ ግለሰቦችን በስብስቡ ማካተት ግድ ይለዋል። ይህም የጋራ ወደሆነ ጊዜያዊ አስተዳደር ሊመራ የሚችል ሲሆን ይህም የሽግግር መንግስት በጊዜ የተገደበ መሆን ሲገባው ዋነኛ ሃላፊነቱም የተቋማትን ለውጥ መምራትና እውነተኛ እርቅ እንዲመጣ መስራት እንዲሁም ነጻና አሳታፊ ምርጫ እንዲካሄድ መንገድ መጥረግ ሊሆን ይገባል።

የሽግግር ጊዜ ፍትህ ለማስፈን እንቅስቃሴ ማድረግም የዚህ ሂደት አካል መሆን የሚገባው ሲሆን ይህም የመጨረሻ ግቡ ማህበረሰባዊ ድነትን ማረጋገጥና አጥፊዎችን ለህግ ማቅረብ መሆን ይገባዋል። በተጨማሪም የክልሎች የጸጥታ አካላትን ሚና መደንገግ፣ ብሄራዊ ጦሩን እንደ አዲስ ማዋቀርና የእዝ ሰንሰለቱን መበየን ተጨማሪ ስራዎቹ ሊሆኑ ግድ ይላል። አለም አቀፍ አካላት ይሄንን ሂደት በገንዘብና በቴክኒክ ማገዝ ይገባቸዋል፡
፡

ይህ ሁሉ እንዲሳካ ግን ሁሉም አካላት መራሩን ሀቅ ሊጋፈጡት ግድ ይላል። ጠ.ሚሩ በትግራዩ ጦርነትና ተያያዥ ሰብአዊ መብት ጥሰት ምክንያት ቅቡልነታቸው እጅጉን መሸርሸሩን ማመንና መቀበል ይገባቸዋል። አብይና ብልጽግና ፓርቲ ብቻውን እንደመንግስት የሚቀጥልበት ሁኔታ አክትሟል ማለት ይቻላል። የትግራዩ ሃይሎች በአንጻሩ በ27 አመቱ የኢህአዴግ ዘመን በነበሩ ችግሮች ምክንያት አብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል እንደ ቀድሞ ዘመን የስልጣን እርካብ ተፈናጠው እንዲቆዩ ፍላጎት የሌለው መሆኑን ነው። ሁለቱም አካላት ምናልባት ጦርነቱን በጦር ሜዳ ድል እንፈታዋለን ብለው ያስቡ ይሆናል ነገር ግን ዘለቄታዊ ሰላም ፈጽሞ ሊያረጋግጡ አይችሉም።

የኢትዮጵያው ጦርነት አስከፊና አውዳሚ ከመሆኑም በላይ ሃገሪቱን የመበታተን አደጋ ጋርጦባታል። አሁን ከመቼውም ጊዜ በላይ የሃገሪቱ ፖለቲከኞችና ልሂቃን ከራሳቸው ጥቅምና ክብር ይልቅ ለሃገሪቱ ሰላምና የግዛት አንድነት መስራት የሚገባቸው ጊዜ ላይ እንገኛለን። ጊዜው እየሄደ ነው። ከመቼውም ጊዜ በላይ ለፖለቲካዊ መፍትሄና ስር ለሰደዱት ቁርሾዎች እልባት ማግኘት የኢትዮጵያውያን የቤት ስራ ይሆናል።